# የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚ ፖሊሲ ያስከተለው አሉታዊ ውጤት በኢትዮጵያ!!

- በአገሪቱ ውስጥ በዐመት የሚመረተው የኢንዱስትሪ፣ የእርሻና የአገልግሎት አጠቃላይ ውጤት ወይም በእንግሊዘኛው (GDP) እየተባለ የሚጠራው በአሃዝ ሲተመን $ 76.9 ቢሊዮን ነው። ይህ እንግዲህ ለአንድ መቶ ሚሊዮን ህዝብ ነው።
- ሰማንያ ሚሊዮን የህዝብ ቁጥር ያላት ጀርመን በዐመት $ 3. 577 ትሪሊዮን የምርት ውጤት (GDP) ታመርታለች። አንድ ሰው በነፍስ ወከፍ በዓመት $ 43,000 ያገኛል።
- ይህ ልዩነት በራሱ ብዙ ነገሮችን ይገልጻል። ያለንበትን የሰማይና የመሬት ልዩነት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ይህ እንግዲህ የከተማዎችን አገነባብ፣ የባህል ሁኔታና የህዝቡን ኑሮ ሳያካትት ነው።
- ኢትዮጵያ በየዐመቱ የምታመርተው ጠቅላላ ምርት በህዝቡ ብዛት ሲካፈል፣ በነፍስ-ወከፍ የሚደርሰው $783 ብቻ ነው። ይህ ግን ሀቁን የሚያሳየን አይደለም። በሌላ አነጋገር እያንዳንዱ ይህን ያህል ይደርሰዋል ማለት አይደለም። ለምሳሌ በኢንፎርማልና በሰብሲስተንስ መስክ የሚሳተፈውና አብዛኛው በልመና የሚተዳደረውና ስራ የሌለው ሁሉ ይህን ያህል በዐመት ያገኛል ማለት አይደለም።
- ባለፉት 27 ዐመታት በሀብታምና በደሀው መሀከል፣ በተለይም በአዲስ አበባ የሚኖረው ህዝብ መሀከል ከፍተኛ የሆነ የሀብት ልዩነት አለ።
- ለምሳሌ በአዲስ አበባ ውስጥ የሀብት ክፍፍል ልዩነት በጂኒ ኮፊሺየንት አለካክ 0.47 በመቶ እንደሆነ ይታወቃል። ይህም ማለት አብዛኛው ሀብት በጥቂቶች እጅ የተያዘና፣ መግዛትና መጠቀምም የሚችለው በጣም ጥቂት የሆነው የህብረተሰብ ክፍል ብቻ ነው።
- በአገሪቱ ውስጥ ድህነት ከመስፋፋቱ የተነሳ፣ አስፈላጊው ለሰውነት ገንቢ በሆኑ የምግቦች እጥረት የተነሳ አገሪቱ $ 4.7 ቢሊዮን ታጣለች።

# የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ...

- ይህ የገንዘብ መጠን 16.5 በመቶ የሚሆነው ጂዲፒ ያክላል ማለት ነው።
- በዚህም ምክንያት የተነሳ ከአምስት ህፃናት ውስጥ ሁለት የሚሆኑ ህፃናት ነገሮችን የመረዳት ችግር አለባቸው፤ ወይም የማሰብ ኃይላቸው በጣም ዝቅ ያለ ነው።
- ከአስፈላጊው የምግብ ዐይነቶች( ቪታሚን፣ ሚኒራልስና ፕሮቲን) ማነስ ጋር በተያያዘ የሚሰቃየው ህፃናት ከጠቅላላው ውስጥ 80% የሚሆነው የህክምናና የምግብ ዕርዳታ አይደረግለትም።
- በዚህም ምክንያት የተነሳ 20 በመቶው የህፃናት ሞት ከአስፈላጊው የደዮት እጥረት ጋር የተያያዘ መሆኑን በኢኮኖሚክ ኮሚሽን ኦፍ አፍሪካና በተባበሩት የዓለም አቀፍ የምግብ ፕሮግራም (WFP) ጥናት ተደርሶበታል።
- እንደሚነገረንና እንደሚባለው በተለይም በአለፉት አስር ዐመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ፈጣን ዕድገት ከሚታዩባቸው አገሮች አንዱ ሲሆን፣ ይህ ዕድገት ከተጨባጩ የኢትዮጵያ ጋር የሚጣጣም አይደለም።
- የዚህ ዋናው ምክንያት የኢኮኖሚው ዕድገት በአገልግሎት መስኩ ላይ ስለሚመካ ነው።
- ለምሳሌ የእርሻው መስክ ከጠቅላላው ጂዲፒ 46% ሲይዝ፣ የአገልግሎት መስኩ 43%፣ ኢንዱስትሪ 11%
  ብቻ ይይዛል።
- የድህነቱ መጠን በተወሳሰበ የማቲማቲክ ስሌትና በዱቄት ዕደላ ከ55% ወደ 39% ዝቅ ብሏል ቢባልም፣ የአብዛኛው ህዝብ ገቢ በቀን ከ$ 1 አይበልጥም።
- በዚህም የተነሳ አዲስ አበባ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛውን የቆሻሻ የህዝብ መኖሪያ ያለባት ከተማ ነች። 80% የሚሆነው የአዲስ አበባ ህዝብ በቆሻሻ ቦታ(Slums Area) ይኖራል። ፊልም...


# የህክምና ዕድል የማግኘት ጉዳይ !

- ኢትዮጵያ ከሌሎች በማደግ ላይ ናቸው ከሚባሉ አገሮች ጋር ስትወዳደር በጣም ደካማ የሆነ የህክምና አወቃቀርና ስርጭት አላት።
- ለዚህ ዋናው ምክንያት የአገሪቱ ደካማ የሆነ የኢኮኖሚ አወቃቀርና አደረጃጀት ነው፣ እንዲሁም ደግሞ የተበላሸ የመንገድ አሰራርና፣ አብዛኛው ህዝብ ተሰበጣጥሮና ከመንገድ ርቆ መኖር ነው።
- በዓለም አቀፍ የጤና ድርጅት ጥናት መሰረት በጠቅላላው በአገሪቱ ውስጥ 1936 ሀኪሞች ሲኖሩ፣ 100 000 ታማሚዎች 2.6 ሀኪሞች ይዳረሳል ማለት ነው።
- በተመሳሳይ በተደረገ ጥናት መሰረት ቺካጎ ከተማ ብቻ እየሰራ የሚኖረው የኢትዮጵያዊ ሃኪም ቁጥር በአገሪቱ ውስጥ ከሚኖረው ጠቅላላ ሀኪም በቁጥር ይበልጣል።
- በጠቅላላው በአገሪቱ ውስጥ 195 ሆስፒታሎች ብቻ ሲገኙ፣ ከነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ በአዲስ አበባ(41)፣ የደቡብ ክልል እየተባለ በሚጠረው ክፍል(45)፣ በኦሮሞ ክልል(31)፣ በትግሬ ክልል(18)፣ በአማራ ክልል ደግሞ 23 ሆስፒታሎች ይገኛሉ።
- በዚህም ምክንያት የተነሳ 80 በመቶ የሞት ምክንያት ከህክምና ጉድለትና ለጤንነት ገንቢ የሆኑ ምግቦች ጋር የተያያዘ ነው።
- በሀኪም ወይም በክሊኒክ አለመስፋፋት የተነሳ 94% የሚሆነው ህጻን ቤት ውስጥ የሚወለድ ሲሆን፣ 61% የሚሆኑ አዋላጆች ከልምድ በስተቀር በቂ ስልጠና ያላገኙ ናቸው።
- ከሚያረግዙት ውስጥ 28% በታች ብቻ ነው አልፎ አልፎ የህክምና ዕርዳታ የሚደረግላቸው።
- ከሚያረግዙት 14 ሴቶች እያንዳንዱ በህክምና ጉድለት የተነሳ ለሞት የተጋለጠች ነች።


# ታይቷል የተባለው የኢኮኖሚ ዕድገት ሊቀርፍ ያልቻላቸው ችግሮች!

- 54 % የሚሆነው ከጠቅላላው የአገሪቱ ህዝብ ውስጥ ንጹህ ውሃ የማግኘት ዕድል የለውም።
- 87.6% የሚሆነው መጸዳጃ የለውም።
- 85.7% የሚሆነው ህዝብ የኤሌክትሪክ ኃይል የማግኘት ዕድል የለውም።
- 89.6% የሚሆነው ህዝብ የምግብ መቀቀያ ነዳጅ ወይም ዘይት ማግኘት አይችልም።
- ከንፅህናና ከአስፈላጊው ዳዬት እጦት የተነሳ ከተወለደው ስምንት ህጻናት ውስጥ አንዱ አምስት ዐመት ሳይሞላው ይሞታል።
- ለመወለድ ከተቃረቡት ህጻናት ውስጥ ከ13 እያንዳንዱ ከመወለዱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ይሞታል
- ወደ ትምህርት መስኩ ስንመጣ 64.9% የሚሆነው ለትምህርት የደረሰ ልጅ ትምህርት ቤት የመግባት ዕድል የለውም።
- በመንግስት ትመና መሰረት የድህነት መጠኑ ቀንሷል ቢባልም አሁንም ቢሆን 38.7% የሚሆነው ከድህነት መለኪያ በላይ በታች እንደሚኖር ይታወቃል።
- በሌላ ትመና ደግሞ ከ90 ሚሊዮን ውስጥ 90% የሚሆነው አስፈላጊውን የቪታሚን፣ የሚኒራልና የፕሮቲን ነክ ምግቦች የማግኘት ዕድሉ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ይነገራል።
- በዚህም የተነሳ አንድ ሰው ሊኖር የሚችለው አማካይ ዕድሜ 57 ነው።
- 1.3 ሚሊዮን የሚሆን ሰው ኤችአይቪና በኤይድስ የታመመ ነው።
- 50%ብ የሚሆነው ለስራ የደረሰ ወጣት በስራ እጦትና በስራ ፈትነት ጊዜውን ያባክናል።

# የየመስኩ አስተዋፅዖ ከጠቅላላው ምርት ውስጥ(GDP) !



# በመንግስት በኩል የሚሰጠው ተጨባጩ የኢኮኖሚ ዕድገት ባለፉት 15 ዐመታት !




# በእርግጥ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለፉት 27 ዐመታት አድጓል ወይ ?

- በዓለም የኢኮኖሚ ፎረም (WEF) መሰረት አንድ አገር ተወዳዳሪ የሆነ ኢኮኖሚ እንዲኖራት ከተፈለገ 12 መሰረታዊ(12Pillars) ነገሮችን ማሟላት አለባት።
- ይኸውም፣ 1. ሰፋ ያለ በጠቅላላው አገር ውስጥ የተቋቋመ ኢንስቲቱሽን፣ 2. የመመላለሻና የመገናኛ ሁኔታ፣ 3. አመቺ የሆነ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ፣ 4. የህክምናና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ጉዳይ፣5. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የማስልጠኛ(Training)ቦታ፣6. የተቀላጠፈ መገበያያ ቦታ፣7. ስራ ፈላጊውን የስራ ዕድል ሊሰጥ የሚችል የተቀላጠፈ የኢኮኖሚ አወቃቀርና ኤጀንሲዎች፣ 8. የተቀላጠፈ የባንክና የፊናንስት ሲስተም፣9. የቴኮኖሎጂ ብቃትነት፣10. ሰፋ ያለ ገበያ፣ 11. የተወሳሰበ የንግድ ስርዓት፣12. ፈጠራ።
- አደገ እየተባለ የሚወራለት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከነዚህ ውስጥ አንዳቸውንም አያሟላም።
- ከላይ በተዘረዘሩት መለኪያዎች መሰረት፣ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ 121ኛውን ስትይዝ፣ ከአፍሪካ ደግሞ 22ኛውን ቦታ ትይዛለች።
- የዓለም ኢኮኖሚ ፎርም ለምሳሌ ውብ ውብ ባህላዊ ከተማዎች መኖርን አይጠቅስም። በተለይም በደንብ የተገነቡና የተስፋፉ ከተማዎች ከሌሉ ሰፋ ያለ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማካሄድ አይቻልም።

# ለኢኮኖሚው ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያስገኘው የአገልግሎት መስኩ ሁኔታ !


## ዕድገት በመቶ 2006-2017




# የውጭ ንግድና የዕዳ ጉዳይ !

- የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በተለይም ህወሃት በሚገዛበት ዘመን በፍጥነት አደገ ቢባልም፣ ወደ ወጭ የሚላከው ምርት አሁንም 90% የሚሆነው በእርሻ ውጤት ላይ የተመረኮዘ ነው።
- ይህም የሚያሳየው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለፉት 27 ዐመታት የተቅዋም ለውጥ( Structural Transformation) ለማየት አልቻለም።
- በዚህም ምክንያት፣ ወደ ውጭ የሚላከው የምርት መጠን ቢጨምርም የንግድ ሚዛኗ በከፍተኛ
- ደረጃ ተናግቷል። እንደ የአሰላሉ የውጭ ንግድ ሚዟኗ በ 2017 $ 13.2 ቢሊዮን ይደርሳል በዚህም ምክንያት የተነሳ አገሪቱ አሁንም በዕዳ እንደተተበተበች ነው።
- ጠቅላላው የዕዳ መጠን አገሪቱ ከምታመርተው ጋር ሲወዳደር 24.1% ይይዛል።
- የጠቅላላው ዕዳ መጠን ከኤክስፖርት የሚገኘውን ገቢ 97.1% ይይዛል። ከጠቅላላው የአገሪቱ ምርት ውስጥ 4.1% ለዕዳው ግልጋሎት በየዐመቱ ይከፈላል።
- በአቢይ አህመድ አምስት ዓመት የአገዛዝ ዘመን ይህ ሁኔታ በፍጹም አልተለወጠም።
- አቢይ አህመድ አሁንም ቢሆን ከኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለመላቀቅ ባለመቻሉ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ እየባሰበት የመጣ ነው።

# ወደ ውጭ የሚወጣውና ወደ አገር ቤት ውስጥ የሚገባው ከጠቅላላው ምርት(GDP) በመቶ ሲተመን !




# የኢትዮጵያ የውጭ ንግድ ሚዛን እ.አ.አ ከ2007-2017 ዓ.ም ብቢሊዮን የአሜሪካ ን ዶላር




| ዓ.ም | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | 2011 | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2917 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 0 | -4,5 | -6,7 | -6,1 | -6,3 | -6 | -8,5 | -9,1 | -12 | -14 | -14 | -13 |


# የውጭ ዕዳ በቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር



# የኢኮኖሚው ዕድገት አሉታዊ ገጽታ- የመኖሪያ ቦታ በአዲስ አበባ!



# የሚያድጉ ልጆች የኑሮ ሁኔታ- የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊስ ውጤት !



# አዲሱ ሀብታም የህብረተሰብ ክፍል !



# የግሎባላይዜሽን መዘዙ- ሥነስርዓት ሳይሆን ቀውስ መፍጠር!



# የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲ አስከፊ ገጽታው !



# የኒዎ-ሊበራል የኢኮኖሚ ፖሊሲ አዲስ የአፎፎር ፍልስፍና- አገር ማፈራረስ!



# ስለ አንድ አገር ኢኮኖሚ በምናወራበት ጊዜ በጭንቅላት መያዝ ያለባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች !

- ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔና ጤናማ የኢኮኖሚ ዕድገት የአንድን አገርና ህዝብ ዕድል ወሳኞች ናቸው !
- ኢኮኖሚ ወደ ተራ ንግድ ተለውጦ መታየት ያለበት ጉዳይ ሳይሆን አንድን አገር ወይም ህብረተሰብ መገንቢያ መሳሪያ ነው!!
- ስለሆነም ኢኮኖሚ ማለት አንድን የተፈጥሮ ሀብት በሰው ጉልበት፣ በኃይልና በማሽን መለወጫ ዘዴ ነው!!
- ይህም ማለት ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔ የግዴታ ከሌሎች የዕውቀት ዘርፎች ጋር የሚያያዝ ነው!!

- ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔ ካለሳይንስና ካለቴክኖሎጂ፣ እንዲሁም ካለማኑፋክቱር በፍጹም ሊታሰብ አይችልም!!

- ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔ በቦታና በጊዜ የሚካሄድ ነው። በደንብ የታቀዱ ከተማዎችና መንደሮች በሌሉበት አገር ውስጥ ስለኢኮኖሚ ዕድገት ማውራት አይቻልም !!
- ኢኮኖሚያዊ ክንዋኔ በመሰረቱ የአንድን ህብረተሰብ መሰረታዊ ፍላጎቶች እንዲያሟላ ሆኖ መታቀድ አለበት !!
- ማለትም ምግብ፣ ንጹህ ውሃ፣ ቤት፣ መቀቀያና መብራት፣ ክሊኒኮችና ሀኪምቤቶች እንዲሁም ትምህርት ቀድመው መሟላት ያለባቸው ጉዳዮች ናቸው !! እነዚህ ሳይሟሉ ስለኢኮኖሚ ዕድገት ማውራት አይቻልም!!
- ስለሆነም አንድ መንግስት ተግባራዊ የሚያደርገው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለአንድ አገር ዕድገት ወሳኝ ነው!!

ፈቃዱ በቀለ

February 15, 2023